# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

1ki Diro Kiiro 11

Hawaasa, Arfaasa 1, 2013 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩

ሀዋሳ፣ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም



**Amado**

**Wodhote Kiiro 11/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Dagoomu Fayyimma Institiyute Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho ……. Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፲፩/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ………. ገጽ….**


## WODHOTE KIIRO 11/2013

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Dagoomu Fayyimma Institiyute Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho**

Qoqqowu giddo Poletiku, miinjunna dagoomitte ikkito aana kaajjado hekko kalaqqara dandiitanno kakkadishshu dhibba, mannu loosinonna kalaqamu dano ikkitinori kalaqantara dandiitannota balaxe heda, gargaranna badhera qolate gaarammanni raga leellishshano fayyimmate intelegense uurrinshanna kalaqantannota haaronna albaanni noo dhiwanna hojjimmatenni woy gobbatenna kalqete heedhanno xiinxallote uurrinshanna

## ደንብ ቁጥር ፲፩/፳፻፲፫

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ**

በክልሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ወረርሽኝ፣ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ክስተት መተንበይ፣ የመከላከልና መቀልበሻ አቅጣጫ ሊያሳይ የሚችል የጤና ኢንቲለጀንሲ ተቋም እና የሚከሰቱ አዳዲስና ነባር በሽታዎችን በተናጠል ወይም በትብበር ከአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የምርምር እና ላቦራቶሪዎች ጋር በመተባበር በፍጥነት ሊለይና መፍትሄ ሊሰጥ የሚችል ተቋም


**Mittu Waagi ….**
*ያንዱዋጋ*

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

laaboraatoore ledo halamatenni rakke baddannonna qarra tirtanno uurrinsha qoqqowinkera hasiissinohura;

Qoqqowu giddonna wole qoqqowubbara noo yuniversite hattono kalqete uurrinshubba qoqqowinkera ha’rissara hasidhanno xiinxallo qoqqowinke daga horaameessimma agarsiissannonna balaxote illachishsha hasidhanno fayyimmate mitiimma badatenni amanyootu deerra agartino qarra tirtanno xiinxallo assa; qarra tirtanno xiinxaallasine burqitannonna kalqetenni heewisamaano ikkite qoqqowonna gobba horameeyye assatenni ilamate sufishsha qaroonsa, buusansiisanna massaga hasiissinohura;

Haaru dhibbi kalaqamanna bashsho noohu galagalcho lexxanni qoqqowinkera leellasira, laboratoorete mereershi jawa woxenna jajja gashshitannorenna seerunni tantanama hoogansanni seeri-galtino heedhannonsa gede assatenni derru derrunkunni afantanno xagishshu uurrinsha uytanno xagishshu owaante isilanchimmanna deerrase agadhitinota ikkitanno gede giddoydinna gobbaydi isilanchimmate qorqorshanna dhuku kaajjishshate looso loosanno uurrinsha uurrisa hasiissinohura;

Haaro tekinoolooje hinkiilatenni, eessatenni, horonsi’ratenninna halashshatenni xagishshu owaante tajetenni irkinse dagoomu fayyimmate owaante aate dandiinanni gede dagoomu fayyimmate dano gargara, balaxe qorowisiisa, qixxaawa, kakkadishshu akatinni kalaqantanno

ለክልሉ በማስፈለጉ፤

በክልሉ ውስጥ እና በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተቋማት በክልላችን ሊያካሂዱት የሚፈልጉትን ጥናት የክልሉን ህዝብ ጥቅም የሚያስጠብቁና ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ የጤና ችግሮችን በመለየት የሥነ ምግባር ደረጃዎችን የጠበቁ ችግር ፈቺ ምርምሮች ማድረግ፣ ችግር ፈች ተመራማሪዎች እየፈለቁ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ በመሆን ክልሉንና አገሪቱን ተጠቃሚ በማድረግ የትውልድ ቅብበሎሹን ማሳለጥ፣ ማስተባበርና መምራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

አዳዲስ የበሽታ ክስተቶች እና ድሮ የነበሩ እንደገና እየተባባሱ ያሉ የጤና እክሎች በክልሉ እየታዩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የላቦራቶሪ ማዕከላት ከፍተኛ የሃብትና ንብረት የሚያስተዳድሩና በህግ ያልተደራጁ በመሆናቸዉ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው በማስቻል በየደረጃው ያሉ የሕክምና ተቋሞቻችን የሚሰጡትን የሕክምና አገልግሎት ጥራቱንና ደረጃዉን የጠበቀ እንዲሆን የውስጥና የውጭ የጥራት ቁጥጥር እና የአቅም ግንባታ ሥራን የሚሰራ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፣

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳት፣ በማስገባት፣ በመጠቀም እና በማስፋት፣ የሕክምና አሰጣጡን በመረጃ ላይ የተመሰረተ የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎች መከላከልና መቆጣጠር (ቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ ዝግጁነትና ምላሽ፣ በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ቬክተር ወለድና ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች)፣ የኅብረተሰብ ጤና

vekitere-qaltannorenna illacha tuga hasidhannore tropikaale dhiwana gargaranna qorqora, dagoomu fayyimma xiinxallo, tekinooloojete reekkonna laboratoorete mereersha waaxatenni mitte kaajjado qoqqowu dagoomu fayyimmanna xiinxallo institiyute uurrisa hasiissinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma jeefisiisaanote amaale mini jeefisiisaano bissa uurrisate, biilloonyenna loosu qeecha murate fulino lallawu kiiro 3/2012 quwa 10 cinaancho quwa 12 iima uynoonnisi biilloonyi garinni tenne wodho fushshino.

**1. Harancho Umo**

Tenne wodho "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Fayyimmate Institiyute Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho Kiiro 11/2013" yine xawinsara dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro aanno gede assa hooguro tenne wodho giddo:

1. **"Fayyimmate Owaante"** yaa fayyimma qawaaxxisa, dhibba gargadha, hurretenna haaroo'mate xagishsha, xaggate laalchonna shiqishsha, dagoomunnita hedeweelcho fayyimmate dano qorqora, dagoomu fayyimma xiinxallonna laboratoore hattono wole fayyimma agarate ledo xaaddanno owaante kamaltanno;
2. **"Xiinxallo"** yaa buqqeete egenno

ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር እና የላቦራቶሪ ማዕከሉን በማዋሀድ አንድ ጠንካራ ክልላዊ የኅብረተሰብ ጤና ምርምር ኢንስቲቲዩት ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት መስተዳደር ምክር ቤት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፲፪ ድንጋጌ ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፲፩/፳፻፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1 **"የጤና አገልግሎት"** ማለት ጤናን የማበልጸግ፣ በሽታን የመከላከል፣ የፈውስና የተሃድሶ ሕክምናን፣ የመድኃኒት ምርትና አቅርቦት፣ የድንገተኛ የኅብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር፣ የኅብረተሰብ ጤና ምርምርና ላብራቶሪ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ጤናን የመጠበቅ አገልግሎትን ይጨምራል፤

2 **"ምርምር"** ማለት አዕምሯዊ ዕውቀትን በመጠቀም አዲስ ነገር ለማግኘት፣

horonsi'ratenni haaro coye afi'rate, qineessate, hayyonna loonsanni doogga kalaqate sayinsaawe hayyo horonsi'ratenni assinanni xiinxallonna buuxo ikke manchi beetti egenno bowirsatenni fayyimmate mitiimma tirtannonna heeshsho woyyeessitanno millimillooti;

3. **"Tekinooloojete Reekko"** yaa industurrate, yuniverstubbate, mootimmatenna wolootu uurrinsha mereero assinanni ogimmate, egennote, tekinooloojete, laashshinanni hayyonna laalchu akeeka soorri'rate ha'rinsho ikke gumisino sayinsaawenna tekinooloojete lopho horaameeyyete iillitanno garanna horaameeyyeno tekinolooje haaru laalchira, ha'rinshora, hororanna uduunnira woy owaantera soorritanno ha'rinshooti;
4. **"Dagoomu Fayyimmate Dano Gargaranna Qorqora"** yaa dagoomu fayyimma mitiimma ajishate assinanni fayyimmate lao, himanate gara, danote gara bada, gargara, qixxaawa, hasiissanno dawaro aa, qorqoranna dagoomu fayyimma dano hekkonni rahe woyyeessate ha'rinshooti;
5. **"Analaytikete Fonqolsha"** yaa sagalete, wayinna wole angannire fayyimmate yaaddonni keeraancho ikkansa fonqolshunni buuxate;
6. **"Riferaale Analaytikete Fonqolsha"** yaa wole sagalete, wayinna qarqaru

ለመተንተን፣ ዘዴዎችንና አሰራሮችን ለመፍጠር ሳይንሳዊ ዘዴን በመጠቀም የሚደረግ ጥናትና ምርመራ ሲሆን የሰው ልጆችን ዕውቀት በማጎልበት የጤና ችግሮችን የሚፈታና ኑሮን የሚያሻሽል እንቅስቃሴ ነው፤

3 **"የቴክኖሎጂ ሽግግር"** ማለት በኢንዱስትሪዎች፣ በዩኒቨርስቲዎች፣ በመንግሥትና ሌሎች ተቋማት መካከል የሚደረግ የሙያ፣ የዕውቀት፣ የቴክኖሎጂ፣ የአመራረት ዘይቤዎችን፣ የምርት ናሙናዎችን የመለዋወጥ ሂደት ሆኖ በውጤቱም ሣይንሣዊ" የቴክኖሎጂ ዕድገቶች ከተጠቃሚ የሚደርሱበትና ተጠቃሚውም ቴክኖሎጂውን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ ጥቅም፣ ቁሳቁስ ወይም አግልግሎት የሚቀይርበት ሂደት ነው፤

4 "**የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎች መከላከልና መቆጣጠር"** ማለት የኅብረተሰብ ጤና ችግሮችን ለመቀነሰ የሚደረግ የጤና ቅኝት፤ የመተንበይ፤አደጋውን የመለየት፤ የመከላከል፤ የመዘጋጀት፤ ተገቢ ምላሽ የመስጠት፤ የመቆጣጠርና ከኅብረተሰብ ጤና አደጋ ተፅእኖ ቶሎ የማገገም ሂደቶች ናቸው፤

5 **"አናሊቲካል ምርመራ"** ማለት የምግብ፤ የዉሃና ሌሎች መጠጦች ከጤና ስጋቶች ነጻ መሆናቸውን በምርመራ ማረጋገጥ ነው፤

6 **"ሪፈራል አናላቲካል ምርመራ"** ማለት ከሌላ የምግብ፣ የዉሃና የአከባቢ ናሙና ምርመራ

akeeki fonqolshi laboratoorubba dhuki aleenni ikkinohanna ledote isilanchimmate buuxo hasi’ranno fonqolshu danaaati;

7. **“Riferaale Diyaginostikete Fonqolsha”** yaa wole laboratoore loossara dandiitannokki fonqolshu dana woy wole laboratoorera loosame ledote buuxo hasi’ranno fonqolshu danaaati.

3. **Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni worroonnihu horosi garinni wole koo-teemmano hanqafannoho.

4. **Jeefishshi Mami-geeshsha**

Tenne wodho woro hasiisanno garinni qoqqowu giddo taqu taqunku afantanno dagoomu fayyimma handaarrarano jeefishshu noote.

5. **Qara Borro Mine**

Institiyutenihu qaru borrote mini Hawaasi quchumira ikkanna hasiishshu garinni qoqqowu giddo sinu borrote mini hee’rasera dandaanno.

6. **Institiyutete Hexxo**

Institiyutete konni woroonni noo hexxo heedhannose:

1. Qoqqowu deerrinni fayyimmate xiinxallo ajanda kaima assi’ratenni balaxote illacha tunganni fayyimmate mitiimma aana xiinxallo assa; sayinsaawenna tekinoojikaawe egenno burqisatenni,

ላብራቶሪዎች አቅም በላይ የሆነና ተጨማሪ የጥራት ማረጋገጫ የሚያገልግ የምርመራ አይነት ነዉ፡፡

7 **“ሪፈራል ዲያግኖሲትክ ምርመራ”** ማለት በሌላ ላብራቶሪ ሊሰራ የማይችል የምርመራ አይነት ወይም በሌላ ላብራቶሪ ተሠርቶ ተጨማሪ ማረጋገጫ የሚሻ የምርመራ አይነት ነዉ፡፡

**፫ የጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ በአንድ ፆታ የተገለጸው እንደ አስፈላጊነቱ ሴላኛዉንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፬ የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በክልሉ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን በሚገኙ የኅብረተሰብ ጤና ዘርፍ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**፭ ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በሀዋሳ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ የተለያዩ ቅርንጫፎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**፮ የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች**

ኢንስቲትዩቱ ከዚህ በታች የተመለከቱ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1 በክልል አቀፍ ደረጃ የጤና ምርምር አጀንዳ ላይ መነሻ በማድረግ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የጤና ችግሮች ላይ ምርምር ማድረግ፤ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂካዊ ዕውቀትን በማመንጨት፣

gamba assatenninna tuqisatenni dagoomu fayyimma woyyeessa;

2. Dagoomunnita qara qara fayyimmate mitiimma tirate, tekinoloojete irkisamatenni fayyimmate owaantera hasiissanno fayyimmate eo ikkitinore laashshanna dagoomunniwa iillitanno gede assa;
3. Dagoomu fayyimmate dano gargaranna qorqora lanohunni hajo la'annonsa bissa ledo buusamatenni balaxi-lao ha'risatenni, danote yaaddo balaxe bada, ikkado qixxaawo assatenni iillitara dandiitanno dano garunni gargara, dano xaaddurono baqqishsha, qorowishshanna yannite mashalaqqe sayisa, rakkinonna ikkado dawaro aa hattono danotenni gawajjantino dagoomitte kifile fayyimmate dano hekkonni jawaattanno gede assa;
4. Institiyutete laboratoorubba qajeeltino mannu wolqanninna jajjabba tekinoloojenni kaajjisha, qoqqowu deerrinni fayyimmatenna sagalete sayinse laboratoorubba dhuka kaajjishanna islaanchimma noose owaante aa dandiitanno gede assa.

**7. Institiyutete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Institiyutete konni woroonni noo biilloonyinna loosu qeechi hee'rannose:

1. Dagoomu fayyimmanna sagalete amuraate lainohunni qoqqowu xiinxallote

በማሰባሰብና በማሰራጨት የኅብረተሰቡን ጤና ማሻሻል፤

2 የኅብረተሰቡ ዋና ዋና የጤና ችግሮችን ለመቅረፍ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በመታገዝ ለጤና አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ ግብአቶችን ማምረትና ለኅብረተሰቡ እንዲደርስ ማድረግ፤

3 የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎች መከላከልና ቁጥጥርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቅኝት በማካሄድ ሥጋቶችን ቀድሞ መለየት፤ በቂ ዝግጅት በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በተገቢ ሁኔታ መከላከል፤ ሲከሰትም ማንቂያ፣ ማስጠንቀቂያና ወቅታዊ መረጃ ማስተላለፍ፣ ፈጣንና ብቁ ምላሽ መስጠት እንዲሁም የተጎዳውን የኅብረተሰብ ክፍል ከጤና አደጋው ተጽዕኖ በፍጥነት እንዲያገግም ማድረግ፤

4 የኢንስቲትዩቱን ላቦራቶሪዎች በሰለጠነ የሰው ኃይልና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ማጠናከር፤ በክልል ደረጃ የጤናና የምግብ ሣይንስ ላቦራቶሪዎችን አቅም መገንባትና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፡፡

**፯ የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1 የኅብረተሰብ ጤናና ሥነ ምግብን በተመለከተ ክልላዊ የምርምር አጀንዳ ያዘጋጃል፤ በአጀንዳው ላይ የተመረኮዘ ምርምር ያካሂዳል፣ ያስተባብራል፣

ajanda qixxeessitanno; ajandu aana uurrite xiinxallo ha’rissanno; qineessitanno; xiinxallote guma tuqissanno; attamame horote hosanno gede loossanno; loonsoonni xiinxallubba guma keentanno.

2. Dagoomunnita qara qara fayyimmate mitiimma tekinoloojete reekko rumuxxisiisatenni kittiwaate, dhibba buunxanni kitte, sagalete sayinsenna sagalate amuraati xiinxallo gummanna hattono woloota fayyimmate owaantera kaa’litanno fayyimmate eo ikkitinore hasiishshu garinni laashshatenni woy qoqqowu giddo islaanchimmatenni qixxaabbanno gede sayinsaawe irko assitanno.
3. Fayyimma qawaaxxisate, dhibba gargarate, hurretenna haaroo’mate xagishsha halashshate dandiissitanno xiinxallubba fayyimmate amuraati aana assitanno; fayyimmate handaarira adhinanni gargarooshshu qaafo abbitino guma keentanno.
4. Taraabbannonna taraabbannokki dhiwanna, sagalete amuraati, qarqaru fayyimmate agarooshshi, fayyimmate amuraati aananna woloutu fayyimmate ledo xaaddanno hajo aana qoqqowu giddo balaxote lao ha’rissanno.
5. Sagalete gattonna taala hooga abbitanno dhibbi ba”anno doogonna maatete deerrinni saga’late amanyooti woyyaawanno gede kaa’litanno taje



የምርምር ውጤቶችን ያሰራጫል ታትመው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይሰራል፣ የተሰሩ ምርምሮችን ፋይዳ ይገመግማል፡፡

2 ለኅብረተሰቡ ዋና ዋና የጤና ችግሮች የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማስረጽ ክትባትን፣ የበሽታ መመርመሪያ ኪቶችን፣ የምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ ምርምር ውጤቶችን እና ሌሎች ለጤና አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ ግብአቶችን አንዳስፈላጊነቱ በማምረት ወይም በክልሉ ውስጥ በጥራት እንዲመረቱ ሳይንሳዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

3 ጤናን ለማበልጸግ፣ በሽታን ለመከላከል፣ የፈውስና የተሃድሶ ህክምናን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ምርምሮችን በጤናው ሥርዓት ላይ ያደርጋል፤ በጤናው ዘርፍ የሚወሰዱ የመከላከል እርምጃዎች ውጤቶችን ይገመግማል፡፡

4 በተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች፣ በሥነ ምግብ፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ በጤና ሥርዓቱ ላይ እና በሌሎች መሠል የጤና ጉዳዮች ላይ ክልላዊ ቅኝቶችን ያካሂዳል፡፡

5 የምግብ እጥረትና ያለመመጣጠን የሚያስከትላቸውን በሽታዎች የሚወገዱበትን መንገድና በቤተሠብ ደረጃ የአመጋገብ ሁኔታ እንዲሻሻል የሚያስችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፡፡

6 ባህላዊ መድሃኒቶችና ሕክምና ዘዴዎች እንዲሁም በዘመናዊ መድሃኒቶች ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ፍቱንነታቸዉንና

gamba assitanno; xiinxallono ha’rissanno.

6. Baadi xagganna xagishshu hayyo hattono yannite xagga aana xiinxallo ha’rissanno; hursaanchimmansanna keeraanchimmansa buuxantinore budu xagga qixaaabbanno hayyo xiinxallitanno; fayyimmate owaante amuraati giddo eanno gede doogo injeessitanno; la’anno uurrinshuwa ledo halamatenni budu xaggara ikkitanno dubbu jironna towaatanna agara hattono budu xagishshinna uduunni ba”annokki gede assitanno.
7. Xiinxallote amanyoote lainohunni qoqqowu giddo assinanni baalante dagoomu fayyimma xiinxallora fajjo uytanno; ha’runsitanno; qorqortanno; xiinxallote beeqqaano keeraanchimma, tajete amado, xaphoomunni xiinxallote amanyootenna dancha xiinxallote wodho la’anno gaydilayne woy manuwaale qixxeessitanno.
8. Gobbate giddonni ikko gobbate gobbaydi la’annonsa uurrinshuwa ledo waaxame loosate hayyo kaajjitannonna bowirtanno gede assatenni gutu xiinxallubba ha’rissanno; hasiishshu garinni womaashshu irko assatenni xiinxallubba wolootta bissa ha’rissano gede assitanno.
9. Qoqqowu giddo afantanno yuniversitubbanna fayyimmate kolleejjubba ledo buusante xiinxallote looso, konforaansuwa, xiinxallote

ደህንነታቸዉ የተረጋገጠላቸዉ የባህል መድሃኒቶች የሚመረቱባቸዉን ስልቶች ያጠናል፣ በጤና አገልግሎት ስርአት ዉስጥ እንዲካተቱ ያመቻቻል፣ ከሚመለከታቸዉ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለባህል መድኃኒቶች የሚሆኑ የደን ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም የባህል ሕክምናና ዕቃዎች እንዳይጠፉ ያደርጋል፡፡

7 የምርምር ስነምግባርን በተመለከተ በክልሉ በሚካሄዱ በማንኛውም የኅብረተሰብ ጤና ምርምሮች ላይ ፈቃድ ይሰጣል፣ ክትትል ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ የምርምር ተሳታፊውን ደኅንነት፣ አያያዝ፣ በአጠቃላይ የምርምር ሥነ ምግባርን እና መልካም የምርምር አሠራርን የሚመለከቱ ጋይድላይኖችን ወይም ማንዋሎችን ያዘጋጃል፡፡

8 ከሚመለከታቸው የአገር ውስጥና የውጭ አገር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲቀየስ፣ እንዲጠናከርና እንዲዳብር በማድረግ የጋራ ምርምሮችን ይሰራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ምርምሮችን የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት በሌሎች አካላት አማካኝነት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

9 በክልሉ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና የጤና ኮሌጆች ጋር በቅርበት የጋራ ምርምር ስራዎችን፣ ኮንፈረንሶችን፣ አውደ-ጥናቶችንና ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት ይሰራል፤ የኅብረተሰብ አቀፍ የምርምር ማዕከላትን በተመረጡ ቀበሌዎች እንዲደራጁ ይሰራል፡፡

daa"atonna simpoozeeme qixxeessatenni loossanno; dagooma hanqaffino xiinxallote mereershuwa doorroonni olluubbara xintantanno gede loossanno.

10. Garimma noonsa bissa ledo buusamatenni daafote akatinni leeltannorinna doorantino fayyimmate yaaddo lainohunni gargaratenna laote looso ha'rissanno; fatiltanno; yannillaancho mashalaqqe tuqissanno.
11. Dagoomu fayyimma danote reqeccimma xiinxallonna fayyimmate dano yaaddo fatilsha ha'rissanno; baqqeenya kalaqqanno; qorowisiissanno; basete lellite buuxo assitanno; ikkitubba buuxxanno; hasiishshu garinni taje la'annonsa bissira tuqissanno; dagoomano dhibbanna woloota fayyimmate dano lao budesi assi'ranno gede kakkayissanno.
12. Dagoomu fayyimmate dano lainohunni hayyo burqissanno; jefishshu biddissa qixxeessitanno; qixxaambetenna dawarote mixo qixxeessitanno; kaajado waaxamatenna halamate amuraate burqisatenni loosu aana hosiissanno; zoonete, woradahonna olluu deerrinni loosu aana hossanno gede irko assitanno.
13. Kalaqamunni woy mannu loosino korinni dagoomaho fayyimmate dano xaaddanno woyte dawaro uytanno; eo ikkitinore shiqishshanno woy shiqqanno gede assitanno; hasiishshisi garinni deerru deerrunkunni qollanni dawarote looso

፲ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በወረርሽኝ መልክ በሚከሰቱና የተመረጡ ጤና ሥጋቶች በተመለከተ የመከላከልና ቅኝት ስራ ያካሂዳል፤ ይተነትናል፤ ወቅታዊ መረጃ ያሰራጫል፡፡

፲፩ የኅብረተሰብ ጤና አደጋ ተጋላጭነት ዳሰሳና የጤና አደጋ ሥጋት ትንተና ያካሂዳል፤ ያነቃል፤ ያስጠነቅቃል፤ በቦታው ተገኝቶ ምርመራ ያካሂዳል፣ ክስተቶችን ያረጋግጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱም መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፤ ኅብረተሰቡንም የበሽታዎችና ሌሎች የጤና አደጋዎች ቅኝትን ባህሉ እንዲያደርግ በትጋት ያንቀሳቀሳል፡፡

፲፪ የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎችን በተመለከተ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ጋይድላይኖችን ያወጣል፤ የዝግጁነትና የምላሽ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አቅም ይገነባል፤ ጠንካራ የቅንጅትና የትብብር ሥርዓት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዞን፤ በወረዳና በቀበሌ ደረጃም ይኸው እንዲተገበር ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፲፫ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ ምክንያት የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎች ሲከሰቱ ምላሾችን ይሰጣል፣ ግብአቶችን ያንቀሳቅሳል ወይም እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው የሚደረጉ የምላሽ ሥራዎችን ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም የደረሰውን ጉዳት በማጥናት ወደ ነበረበት እንዲመለስ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

qineessitanno, irkissanno; la'annonsa bissa ledo buusante iillitino gawajjo xiinxallatenni bashshowa higanno gede irko assitanno.

14. Kaajjado dagoomu fayyimma danonna kalqete rakko iillishshanno dhiwanna lainohunni gobbate deerrinni sumuumme assinoonni kalqete fayyimmate seerubba loosu aana hosiissanno.
15. Qoqqowu giddo afantanno fayyimmate uurrinsha giddo noo laboratoorubba wolqa aleenni higgino riferaalete, ispeshaalizidenna analaytike hattono buuxote fonqolshi looso loossanno.
16. Qoqqowoho heedhanno dhiwamaano yanna iilitino xagishshu laalchinni owaantete horameeyye assate xaggate guunte fonqolchinanni buusamate mereersha xintitanno.
17. Babbaxxitino gobbaydi gobba xaggate industurubba, qoqqowoho noota ikkado xiinxallote eo ikkitinore laboraatoore, hospitaale, mannu jiro, dhibbanna dhibbu dana la"atenni, xaggate wo'naalshi xiinxallonsanna xaggate gumaamimma aana investimente ha'rissanno gede injo kalaqqanno; egensiisate looso loossanno; xaadooshshe kalaqqanno; waaxantanno; sheemaate e'anno.
18. Xiinxallote hasiisanno balaxi-qajeelsha qeechi-gutamaano bissa ledo waaxante uytanno; xiinxallo ha'rissanno; xiinxallote ha'rinsho ha'runsitanno; gumulsiissanno; xiinxallote guma

፲፬ ከፍተኛ የኅብረተሰብ ጤና አደጋ እና ዓለም አቀፍ ቀውስ የሚያስከትሉ በሽታዎችን በተመለከተ አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የጤና ህጐችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፲፭ በክልሉ ውስጥ ባሉ ጤና ተቋማት ካሉት ላቦራቶሪዎች አቅም በላይ የሆኑ የሪፈራል፣ ስፔሻላይዝድ፣ አናሌቲካል እንዲሁም የማረጋገጫ ምርመራ ሥራዎችን ይሠራል፡፡

፲፮ በክልሉ የሚገኙ ህሙማን ዘመኑ በደረሰበት የሕክምና ውጤት ተጠቃሚ ለማድረግ የመድኃኒቶች ውጤታማነት መፈተሻ ማስተባበሪያ ማዕከል ያቋቁማል፡፡

፲፯ የተለያዩ የውጭ ሀገር የመድኃኒት ኢንዱስትሪዎች በክልሉ ያለውን በቂ የሆኑ የምርምር ግብዓቶች (ላቦራቶሪ፤ ሆስፒታል፤ የሰው ኃይል፤ የበሽታና የበሽታ አይነቶች) ተመልክተው የመድኃኒት ሙከራ ጥናቶቻቸውንና የመድኃኒት ውጤታማነት ኢንቨስትመንታቸውን እንዲያከናውኑ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ የማስተዋወቅ ስራዎችን ይሰራል፤ ግንኙነቶችን ይፈጥራል፤ ያቀናጃል፤ ውል ይዋዋላል፡፡

፲፰ ለጥናቶቹ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ስልጠናዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰጣል፤ ጥናቶችን ያከናውናል፤ ሂደታቸውን ይከታተላል፤ ያስፈጽማል፤ ውጤታቸውን ያሰራጫል፤ ሕብረተሰቡና የጤና ባለሙያዎች የአዳዲስና ዘመናዊ ጥናት ውጤቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

tuqissanno; dagoomanna fayyimmate ogeeyye haaronna yannitte xiinxallo gumi horaameeyye ikkitanno gede assitanno.

19. Qoqqowu fayyimmate xiinxallo mashalaqqete mereershanna laybireere xintatenni xiinxallote marro higama heedhannokki gede assatenni baxxino qeecha fultanno; qoqqowu giddo loosantanno xiinxallora kaa’litanno aye gari mashalaqqete borronna akeeka annimmatenni amadde maarekkitanno; xiinxallaano horonsidhanno gedeno fajjo uytanno.
20. Qoqqowu giddo ha’rinsanni ayeno fayyimmate ledo xaaddanno xiinxallote gumi ripoortubbanna tittirshubba gamba assite wortanno.
21. Qoqqowu giddo noo fayyimmate ogeeyye, fayyimmate rosaanonna dagooma kaa’litanno maxaaffubba, gaydilaynubba, biroosherubba, woraqattanna posterra qixxessitanno; tuqissanno.
22. Qoqqowu giddo luphi yite leeltannonna rosantino fayyimmate dano dagoomu huwanyo afi’ranno gede assitanno.
23. Derru deerrunni hee’ra hasiissanno laboratoorete fonqolshi owaantenna sufishsha, laboratoorete isilanchimma amuraatenna woloota xaande noonsa laboratoorete islaanchimma amuraate diriirsa la’anno haja aana qoqqowu deerrinni laboratoorete poolisenna

፲፱ በክልሉ የጤና ምርምር መረጃ ማዕከልና ላይብሬሪ በማቋቋም የጥናቶች ድግግሞሽ እንዳይኖር በማድረግ ዓይነተኛ ሚና ይጫዎታል፤ በክልሉ ውስጥ ለሚሰሩ ጥናቶች አጋዥ የሚሆኑ ማናቸውንም መረጃ ጽሁፎችና ናሙናዎች በባለቤትነት ጠብቆ ያስቀምጣል፤ ለተመራማሪዎች ግልጋሎት እንዲሰጡ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፳ በክልሉ የሚሰሩ ማናቸውንም የጤና ነክ ጥናት ውጤት ሪፖርቶችንና ዝርዝሮችን አሰባስቦ ያስቀምጣል፡፡

፳፩ በክልሉ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎችን፤ የጤና ተማሪዎችንና ኅብረተሰቡን የሚያግዙ መጽሐፎች፣ ጋይድ ላይንኖች፣ ብሮሸሮች፤ በራሪ ወረቀቶችና ፖስተሮች ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፡፡

፳፪ በክልሉ ውስጥ ጎልተው የሚታዩና የተለመዱ የጤና አደጋዎች ኅብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲይዝ ያደርጋል፡፡

፳፫ በየደረጃው ሊኖር የሚገባውን የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎትና ቅብብሎሽ፣ የላቦራቶሪ ጥራት ሥርፀትንና ሌሎች መሠል የላቦራቶሪ ጥራት ሥርዓት መዘርጋትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ክልል አቀፍ የላቦራቶሪ ፖሊሲ እና መርሃ ግብር ያወጣል፤ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፡፡

፳፬ ተከታታይና ወቅታዊ፤ የክትትልና የድጋፍ ስራ በማከናወን፤ ቁልፍ የላቦራቶሪ ችግሮችን በመለየት፤ መፍትሄ በመቀየስና አቅማቸውን በመገንባት ሁሉም የክልላችን ላቦራቶሪዎች አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ

pirograame qixxeessitanno; loosu aana hosansa ha’runsitanno

24. Sufantinonna yannite ha’runsotenna irkote looso ha’risatenni, qara laboratoorete mitiimmubba badatenni, tirote hayyo burqisatenninna dhukansa kaajjishatenni wo’manti qoqqowinke giddo noo laboratoorubba kalqimmate deerra agadhitanno owaante uytanno gede assitanno.
25. Fayyimmate biiro fushshitanno biddissi kaiminni uytanno owaantera baatooshshe baatisiissanno; gamba yitanno eo institiyutete owaantera hossanno gede assitanno.
26. Jajjaho anna ikkitanno; sheemaate e’anno; su’misenni qaxxartanno; qaxxarantanno.
27. Dagoomu fayyimmate dano qorqoratenna lifixa dawaro aate hosanno rakkote barri woxe gumulsiisanno; rakkote yannara hasiissannore xagishshaho eo ikkitannorenna xagishshu uduunne mareekkite amaxxitanno; gashshitanno.
28. Hexxo jeefisiisate kaa’lannoha wole loossa loossanno.

**8. Institiyutete Tantano**

Institiyutete:

1. Amaalaancho Boordenna xiinxallote amanyoote keentanno Boorde heedhannose;
2. Institiyutete Fayyimmate Biiro shiqishonni somantanno qaru

አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል።

፳፭ ጤና ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ለሚሰጠዉ አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤ የሚሰበስበዉን ገቢ የተቋሙን አገልግሎት ለማሻሻል እንዲዉል ያደርጋል።

፳፮ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ዉል ይዋዋላል፤ በራሱ ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል።

፳፯ ለኅብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ቀልጣፋ ምላሽ ለመስጠት የሚውል የመጠባበቂያ ገንዘብ ያስወስናል፤ በመጠባበቂያነት የሕክምና አቅርቦትና መሣሪያዎች ክምችት ይይዛል፤ ያስተዳድራል።

፳፰ ዓላማዉን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናዉናል።

**፰ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት**

ኢንስቲትዩቱ:-

1 አማካሪ ቦርድ እና የጥናትና ምርምር ስነምግባር ገምጋሚ ቦርድ ይኖረዋል፤
2 ኢንስቲትዩቱ በጤና ቢሮ ኃላፊ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዳይሬክተር ይኖረዋል፤
3 ለስራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፤
4 እንደ አስፈላጊነቱ በስሩ ስራዎችን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ የስራ ሂደቶችን ያደረጃል።

dayrekterenna hasiishshu garinni layinki dayrektere heedhanose;

3. Hattono loosoho hasiissanno wolootu loosaasine heedhannose.
4. Hasiishisi garinni loosu guunte ledate hasiissanno loosu handarra tanta’nitanno.

**9. Amaalaancho Borde Miilla**

Amaalaancho borde miillanna gambasaanchu mootimmatenni somantanno; kiironsano hasiishshisi garinni murantanno.

**10. Amaalaancho Boorde Biiloonyenna Loosu Qeecha**

1. Institiyute xiinxallote poolise istraateejike mixonna wole guulcho hajo aana amaaltanno.
2. Hasiishshu garinni tekinikete komite xintitara dandiitanno.

**11. Amaalaancho Borde Gambooshshe**

1. Amaalaancho borde loosu hasiishshisi bikkinni gambooshshe assitanno.
2. Bordete miillanni bocu aleenni leellituro gambooshshu guutaho.
3. Bordete gumulo huurotenni baxxitanno; huuro lamenkawa taalte gibburo, gambisaanchu aanno huuro hidhitanno.
4. Kuni quwi agaramino gedeenni hee’reenna amaalaancho borde umise gambooshshu amuraati wodho fushshitara dandiitanno.

**12. Qaru Dayrekterichi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

**፱ የአማካሪ ቦርድ አባላት**

የአማካሪ ቦርድ አባላት ሰብሳቢዉን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸዉም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

**፲ የአማካሪ ቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

1 ኢንስቲትዩቱን በጥናትና ምርምር ፖሊሲ፣ ስትራቴጂክ እቅድ እና ሌሎች አንኳር ተቋማዊ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፡፡

2 እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**፲፩ የአማካሪ ቦርዱ ስብሰባ**

1 አማካሪ ቦርዱ ለስራዉ ባሰፈለገ መጠን ይሰበሰባል፤

2 ከአማካሪ ቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባዉ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3 የአማካሪ ቦርዱ ዉሳኔ በድምጽ ብልጫ ይለያል፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4 የዚህ አቀንጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አማካሪ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስርዓተ-ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪ የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1 ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

1. Qaru dayrekiterichi institiyutete qara loosu jeefisaancho ikke institiyutete looso massaganno; gashshanno.
2. Konni quwi cinaancho quwi 1 aana worroonniti xaphooma woro noo gede heedheenna qaru dayrekterichi:
   a) Tenne wodhora quwa 7 hunda worroonniha institiyutete biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisanno;
   b) Qoqqowunnita mootimmate loosaasine seeru wodhi-woro kaima assatenni mootimmate muronni kaajjanno seera horonsi’ratenni institiyutete loosaasine gaamanno, wole wiinni abbanno, gashshanno; geegeesanno.
   c) Institiyutete gumulsiishshu aanti-gedeni istraateeje fushshitanno, diru mixonna bajeette qixxeessanno; fajjinanni woyteno loosu aana hosiisanno.
   d) Institiyutete loosu jeefishshanna shallagote rippoorte qixxeesse Fayyimmate Biirora shiqishanno.
   e) Institiyutete fajjinoonni baajeete loosu pirogramenna faynansete seeri garinni fulo assanno.
   f) Institiyutete Sayiki wogane ledo assitanno xaadooshshira institiyute lekkisanno.
   g) Loosu bilchaantera hasiisanno deerinni biilloonyisinna loosu qeechisi aaninni gama booce wolootu

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተዉ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች ህግን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያዛዉራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

ሐ)የኢንስቲትዩቱ ስትራቴጂዎች፣ የአፈጻጸም መርሐ ግብሮች፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ)የኢንስቲትዩቱን ሥራ አፈጻጸምና ሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቢሮው ያቀርባል፤

ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፤

ረ) ኢንስቲትዩቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) ለሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ በሆነ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በዉክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

institiyutete losaasinera lekkishshunni saysara dandaanno.

**13. Layinki Dayrekterichi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Layinki Dayrekterichi:

1. Institiyutete loossa mixiratenni, tantanatenni, massagatenninna qineessatenni qara dayrektericha kaa'lanno.
2. Qaru dayrekterichinni aamamanno looso loosanno.
3. Qaru dayrekterichi nookki woy loosara dandaannokki yannara iso riqiwe loosanno.
4. Qaru dayrekterichira hundaanchoho.

**14. Bajeettete Buichonna Amado**

1. Qoqqowu mootimmanni gaammanni baajeettenna halamaano bissubbawiinni afi'nanni eo;
2. Institiyutute uyiitanno babbaxxitino owaante yaano laabaraatoorete fonqolshinni, qajeelshunni hattono institiyutete ha'rissanno xiinxallonni gamba assitanno eonni ikkanno.

**15. Baajeettete Diro**

Institiyutennihu baajeettete diri qoqqowu mootimma baajeettete diro ikkanno.

**16. Shallagote Tajenna Qorqorsha**

1. Institiyute wo'manna halaalaancho shallagote taje amadanno.

**፲፫ የምክትል ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት**

ምክትል ዳይሬክተሩ፡-

1 የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

2 በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጡ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

3 ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

4 ተጠሪነት ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል::

**፲፬ የበጀት ምንጭና አያያዝ**

1 በመንግስት ከሚመደብ በጀት እና ከአጋር አካላት ከሚገኝ ገንዘብ፣

2 ኢንስቲትዩቱ ከሚሰጠዉ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ማለትም ከላበራቶሪ ምርመራ፣ ስልጠና እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ ከሚካሄዱ የጥናትና ምርምር ስራዎች ከሚሰበስበው ገቢ ይሆናል፡፡

**፲፭ የበጀት ዓመት**

የኢንስቲትዩቱ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

**፲፮ የሒሳብ መዛግብት እና ምርመራ**

1 ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2 የኢንስቲትዩቱ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር

2. Institiyute shallagotenna woxe la'anno tajubba qoqowu qaru odiitere woy qaru odiiterenni somantanno ogeeyyenni diru dirunni qorqorsha assitanno.

**17. Halamate Gadacho**

Ayeno hajo la'annonsa bissa tenne wodho gumulsiisate halamate gadacho noonsa.

**18. Jeefishshu Nookki Seerubba**

Tenne wodho ledo kiphi yitanno aye wodhonna biddissi woy rosamino asooti tenne wodhonni hanqafantino hajubbara jeefishshu diheeranonsa.

**19. Biddissa Fushsha Lainohunni**

Tenne wodho loosu aana hosiisate hasiissanno biddissuwa biiro fushshate dandiitanno.

**20. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho Maaja 1/2012 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Hawaasa, Arfaasa 1, 2013M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡

**፲፯ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ይህን ደንብ በስራ ላይ እንዲውሉ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፰ ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደምብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡

**፲፱ መመሪያን ስለማውጣት**

ይህንን ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ መመሪያዎችን ቢሮው ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳ ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ሀዋሳ፣ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም

ደስታ ሌዳሞ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ርዕሰ መስተዳድር